የወ/መ/ቁጥር 157421

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ አቶ ፋንታሁን መሀመድ ሰይድ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ጥቅምት 02 ቀብ 2002 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 441(1)(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ነሐሴ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ሲሆን በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/18 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ከፍተኛ ፍ/ቤት ፊት ለፊት ኒያላ ሆቴል አጠገብ በወቅቱ የትራፊክ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ያልተቀደ ቦታ የቆመ መኪና አንዲሄድ በማናገር ላይ የነበረውን የግል ተበዳይ ረ/ሣ ታደሰ ፈለቀ | የተባለውን የለበሰውን የደንብ ልብስ ኮሌታ አንቆ በመያዝ ለመማታት በመጋበዝ የግል ተበዳይ የስ ግዴታውን እንዳይወጣ ያሰናከለ በመሆኑ በፈፀመው የኃይና ማስገደድ ድርጊት ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን እነዚህ ምስክሮችም ሁለቱም የትራፊክ ፖሊስ የሕግ አስከባሪ መሆናቸውን ገልፀው በሰጡት ምስክርነት በክሱ ላይ በተመለከተው ጊዜ፤ ቦታና ሰዓት አንድ መኪና ቆሞ ድርፍት በማውረድ ላይ ሳለ፤ ቦታው የተከለከለ ስለነበር ሹፌሩን መንጃ ፈቃድ አምጣ በማለት ከ/ብል ታደሰ ፈለቀ ለመክሰስ በማናገር ላይ ሳለ ተከሳሽ ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ የትራፊክ ፖሊሱን ለመክሰስ አትችሉም ብሎ በመናገር የሸሚዙን ኮሌታ አንቆ ይዞታል፤ ከዚያ በአካባቢው ላሉ ፖሊሶች ጠርተን ነው ወደ ጣቢያ የወሰድነው በማለት ሁለቱም ምስክሮች በተመሳሳይ መልኩ ስለመሰከሩ ተከሳሽ በተከሰሰበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 441(1)(ሀ) ስር እንዲካለከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብሎ አንድ የመከላከያ ምስክር አቅርቦ ያሰማ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስያዘው ነጥብ በወቅቱ ማለትም ነሐሴ 16 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 10፡30 ሰዓት አካባቢ የግል ተበዳይን አለማነቁን አስረዳለሁ፤ እንዲያውም እነሱ የፖሊስ ኃይል ጠርተው

እንደደበደቡኝ አስረዳለሁ፤ በወቅቱ ከምሰራበት ሆቴል በረንዳ ላይ ቆሞ ስለነበረና ስላየ ይህን አስረዳለሁ በማለት አስመዝግቦ በዚሁ መሰረት ምስክሩ መታላ ፈፅሞ የመሰከረ ሲሆን ቃሉም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ አስተባብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ የመከላከያ ምስክር ቀርቦ እንዳስረዳው በወቅቱ መኪናው ቆሞ ድራፍት ለተከሳሹ የሚወርድ እያወረደ ነበር፤ በዚህ ጊዜ እኔ በረንዳ ላይ ሆኜ እያየሁ ነበር፤ የትራፊክ ፖሊሶች እየፃፉ ነበር፤ ከዚያ ተከሳሽን በምን መነሻ እንደሆነ በማላውቀው ሁኔታ የሆኑ የፖሊስ አባለት መጥተው እየደበደቡ ወስደውታል በማለት የመሰከረ ቢሆንም በወቅቱ ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር በምን እንደተጣሉ ለማስረዳት አልቻለም። የትራፊክ ፖሊስ አባላት በወቅቱ በተከለከለ ቦታ ያቆመውን ሹፌር በማናገር ላይ እያሉ ተከሳሽ ከስራው ውጭ በማይመለከተው ሁኔታ ተከሳሾች ሥራቸውን በአግባቡ እንዳያከናውኑ ስለማድረጉ የተረጋገጠበት ሲሆን በመከላከያ ምስክሩ ግን ይህን አለማድረጉን ያላስተባበለ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 441(1)(ሀ) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያት ባይኖረንም በቅጣት መመሪያው መሰረት ተከሳሽን የሚያርምና የሚያስተምር ቅጣት እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 30 ዓመት ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የትምህርት ደረጃዬ 10 ኛ ክፍል ነው፤ በሆቴል ውስጥ ተቀጥሬ በወር ብር 150.00(አንድ መቶ ሃምሳ ብር) ይከፈለኛል በማለት አመለከተ።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ ከአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ቆይቶ ይቅረብ።

2 ኛ. ቅጣት ለመወሰን ለሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ተቀጠረ።

ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ አቶ ፋንታሁን መሀመድ ሰይድ - ከማረሚያ ቤት ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ቅጣት ለመወሰን ሲሆን የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ቅጣት</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 441(1)(ሀ) /የኃይልና ማስገደድ ድርጊት ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ኩበደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ኩበደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው የግል ተበዳይ ተከሳሹ ላይ ባልደረሰበት ሁኔታና ሥራውን በሚያከናውንበት መካከል ስለሆነ ዝቅተኛ የወንጀል ድርጊት የማይባል ቢሆንም በሌላ በኩል የግል ተበዳይ ሲያናግረው የነበረው ሹፌር ለተከሳሹ ድራፍት እያወረደለት ስለነበር በዚህ መካከል የተፈፀመ ከመሆኑ አንፃር የወንጀል ደረጃው ከባድ ሳይባል ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በሕጉ አንቀፅ 441(1)(ሀ) ላይ የተደነገገው የሚያስቀጣው ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ስለሆነና እርከን ከመወሰኑ በፊት

ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች በቅድሚያ አንዱ መለየት ያለበት በመሆኑ፤ በዚህም መሰረት ተከሳሽ የወር ገቢው ብር 150.00(አንድ መቶ ሃምሳ ብር) ከመሆኑ አንፃር እና ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት አንፃር ተከሳሽን የሚያርመው የእስራት ቅጣት ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ስላመነ በእስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

ይህን መሰረት በማድረግም በወጣው የወንጀል ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ ሺህ ዘጠና አምስት ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተካፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ደረጃ ፈቃደ ስልጣኑ ከሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ቀን እስከ አምስት መቶ ሀምሳ ሁለት ቀን ተኩል ቀላል እስራት ነው።

በዚህም መሰረት የተገኘው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 6 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቃደ ስልጣኑም/range/ ከስምንት ወር እስከ አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት አስር ወር ቀላል እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84 እና 85 እንደተገለፀው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስላላቀረበ ቅጣቱ ከዚህ ከመነሻ ቅጣቱ ከብዶ አልተወሰነም።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከላይ የተወሰነው የእርከን 6 መነሻ ቅጣት ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆነም በመነሻ እርከኑ ላይ የተወሰነው ቅጣት የሚያከብድ ወይም የሚያቀል ምክንያት ያልቀረበ በመሆኑ ከላይ በተገለፀው የአስር ወር ቀላል እስራት ተከሳሽ እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ተከሳሹ እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በማሰብ
   የተወሰነው የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

3 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።